# የትግራይ ሴቶች ማሕበር

# የማሕበረሰብ አገልግሎት

# መመዘኛ ካርድ

## በየም አማካሪ ተቋም

## የተዘጋጀ

ጥቅምት/2001

# መግቢያ

ተጠያቂነት ማለት ስልጣን ላይ የተቀመጡ ሰዎች ለሚያከናውኑት ስራ (ተግባር) ሁሉ ተጠያቂ የሚሆኑበትና ሀላፊነትን እንዲወስዱ የሚገደዱበት ሂደት (ሥርዓት) ነው። በመሆኑም ማሕበራዊ ተጠያቂነት ስንል ተጠያቂና ሀላፊነት የሚሰማው ኣስተዳደርን ለመገንባት ህብረተሰብ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ኣካሄድ ነው።

የኣገልግሎት መመዘኛ ካርድ ኣሰራር ሂደት በህብረተሰብ ተሳትፎ ቁጥጥር ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ የሚጠቀምበት ዘዴም ማሕበራዊ ክትትል (ቁጥጥር)ና የዜጎችን ሪፖርት በመጠቀም ነው። መመዝገቢያ ካርዱ እንደዜጎች ሪፖርት ሁሉ ማህበራዊና ህዝባዊ ተጠያቂነትንና ሃላፊነትን ኣገልግሎት ሰጪዎች የሚያስገነዝብ መሳሪያ ሲሆን አካሄዱና መሠረቱ በህብረተሰቡ የታችኛው ደረጃ ላይ የቁጥጥሩን መረብ የዘረጋ ነው።

አጠቃላይ ዓላማውም የሀገሪቱን የልማት ሂደትና የአገልግሎት አቅርቦትን ለማሻሻልና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በህብረተሰቡ ደረጃ በማሳደግ ብሎም አቅምን ለማጎልበት አከባቢያዊ አስተዳደርን፤ ህብረተሰባዊ መሰረት ያደረገ ድርጅት በመፍጠርና የሴቶች ማህበራትን በሁሉም ደረጃዎች በማጠናከር ነው።

የኣገልግሎት ክትትሉ ግብና ስፋትም በመጀመሪያ ደረጃ ህብረተሰቡ በአገልግሎት አቅርቦት ረገድ ያጋጠሙትን ችግሮች ለይቶ በመረዳት ለተሻለ ውጤት ያበረታታል መነሻ በትግራይ ክልል ሴቶች ማህበር አማካይነት ለፕሮጀክት ጥናት ክትትል የተመረጡት አገልግሎቶች ጤናና ትምህርት ናቸው። የማህበረሰብ ተሳትፎ ውጤት መመዝገቢያ ካርድ ተመራጭ የማህበራዊ ተጠያቂነት መሳሪያ ነው። የዚሁ ጥናት ክፍል ደግሞ ራሱ ህብረተሰቡ ነው።

የአገልግሎቱ ስፋት ክትትልም ለመተግበር የታቀደው በሰባቱ የትግራይ ወረዳዎች ውስጥ ሲሆን በጥናቱ ዶክመንትም የተካተተዉ የማህበረሰቡ መመዘኛ ካርድ የጤናንና የትምህርት ክፍሎችን ብቃት፤ ጥራት፤ አስተማማኝነትና ቅልጥፍናን ይለካል ተብሎ ይገመታል።

የም አማካሪ ተቋም

# 1. ልማትና የህብረተሰብ ተሳትፎ

## 1.1. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋንኛ አላማ የስልጠናው ተሳታፊዎች የዜጎችና የማህበረሰቡ ህጋዊ መሰረት ምን እንደሆነና መብታቸውን ተጠቅመው የክልሉ ባለስልጣናት እና በአገልግሎት የተሰማራው ሰራተኛ ለስራውና ለህዝቡ ያላቸውን ተጠያቂነት ግንዛቤ ለማስጨበጥ የተዘጋጀ ነው። በዚህ በተዘጋጀው የስልጠና መመሪያ ማብቂያ ላይም ተሳታፊዎች፤

- የልማትን መሰረታዊ ዓላማዎች፣
- የልማትና የድህነት ጽንሰ ሀሳቦች፣
- የመልካም አስተዳደርን ባህርያት፣
- የኢፌዴሪ የ1987 ህገ-መንግስት ያስገኘውን መብት፣ የክልሉ ባለስልጣናት ለህዝቡ ያላቸውን ተጠያቂነት፣ ድህነትን ለማስወገድ የተዘረጋውን የተፋጠነና ቀጣይነት ያለው ዕቅድ፣ ሰነድና በምዕተ ዓመቱ ግቦችና መሰረታዊ አገልግሎቶች መካከል ያለውን ግንኙነቶች ግንዛቤ ይጨብጣሉ ተብሎ ይገመታል።

## 1.2. ድህነትና ልማት ምንድን ነዉ?

ድህነት ማለት ሰዎች ልማት ከሚያስገኘው ጥቅም ሁሉ የተገለሉ ማንኛውም እድል የተነፈጋቸውንና ምንም አይነት ገቢ የሌላቸው እንዲሁም የወደፊት እጣ ፈንታቸውን ለመወሰን አቅም የተሳናቸወና ኑሮአአቸውም የጨለመባቸውን የሚያመለክቱ ናቸው። በሰው ልጆች መብት አንጻርም ስንመለከተው ድህነት ከቁሳዊ ባለቤትነት መገለልና በገቢ እጦት ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን ከሰዎች መብት ጥበቃና ከመልካም አስተዳደር እጦት ጭምር ይገለጻል።

ይህንንም በተመለከተ እ.አ.አ በ1999 በኢኮኖሚክስ የኖቤ ሽልማት አሸናፊ የሆኑት ፕሮፌሰር አማርትያ ሴን ልማትን ከሰዎች መብትና ነጻነት ጋር በማያያዝ እንደሚከተለው አብራርተዋል።

"ልማት መታየት ያለበት ሰዎች ሊቀዳጁት ከሚገባቸው የነጻነት ፍሬ አንጻሩ መሆን ይገባዋል። ትኩረትም ከሰዎች ብሄራዊ የምርት ውጤት፤ የገቢ ማደግ፤ ከኢንዱስትሪ ምርት ከቴክኖሎጂ ምጥቀት ወይንም ከማህበራዊ ስልጣኔ ላይ ነው። ልማት የነፃነት እንቅፋቶችን ማስወገድ ይጠይቃል የሚባለው ድህነትን፣ ጭቆናን፣ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ሁኔታን፣ ማህበራዊ ህይወት መነፈግንና አገልግሎት እጦትን ያስቀራል።"

ድህነትን በትክክል ለመረዳት የሰው ልጆች ካላቸው የልማት ተጠቃሚነት መብት አንጻር መታየት ይኖርበታል ድህነት ሲባልም ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ገቢ ብቻ ተደርጎ መወሰድም የለበትም። እንዲያውም ከመሰረታዊ የሰው ልጆች ከልማት የመጠቀም

መብት እጦት፣ የማህበራዊ ፍትህ ችግር፣ የአድልዎ መንሰራፋትና የሰው ልጆች መሰረታዊ መብት መገፈፍ ጋር የተያያዘ ነው።

<u>እንደ</u> እ.አ.አ በ1986 የተካሄደውን የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ የሰው ልጆች ከልማት የመጠቀም መብትን አስመልክቶ የሚከተለውን አውጆ ነበር።

"አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ፣ ባህላዊና፣ ፖለቲካዊ ሂደት አልሞ መነሳት ያለበት በቀጣይ የሰዎች የድህነት ሁኔታ መሻሻልና በአጠቃላይ የህዝቡና የግለሰቦች እንቅስቃሴ፣ ነጻነትና ተሳትፎ ላይ ሲሆን። እነዚህም በልማቱ ዉጤትና ክፍፍል ላይ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው።"

**ልማት የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል፣**

- ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ ሂደትን የሚያካትት፣
- የአጭር ጊዜ ሂደት ሳይሆን በረጅም የጊዜ ሂደት ላይ የተመሰረተ ክስተት፣
- የልማት ዓላማው በህዝቦችና በግለሰቦች የህይወት መሻሻል ዙሪያ ያተኮረ፣
- ልማት የህዝቦችን ቁርጠኛ ተሳትፎ የሚጠይቅ፣
- ልማት ከአድሎ የጸዳ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የዜጎች ጥቅም ላይ ያነጣጠረ መርህን የሚከተል ነው።

በ1987 የጸደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ ህገ-መንግስት የልማት ዓላማም ህዝብን ማእከል ያደረገ ነው። አንቀጽ 43 ወይም 44 ላይ እንደተጻፈው "የልማት ስራ መሰረታዊ ዓላማው የዜጎችን የልማት አቅምና ጥቅም ለማፋጠን ነው።"

**የጋራ ዉይይት**

- ልማትና እድገት፣
- ልማትና መብት፣

ልማት እንደመብት እንዲቆጠርና ግንዛቤም እንዲወሰድበት ያልተቋረጠ ትግልና ጥረት ተካሄዷል። በዚህም እ.አ.አ የ1966 አለማቀፋዊ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ጉባኤ የሰው ልጆች ሊቀዳጇቸው የሚገቡ መብቶችንና ጥቅሞችን ይዘረዝራል። ከነዚህም መካከል የሰው ልጆች ደረጃውን የጠበቀ ኑሮ የመምራት፣ ትምህርት የማግኘትና ጤናን የመንከባከብ መብቶች አሏቸው።

እንደ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ቀና ዕሳቤ መሰረትም ክልሎች የልማት ፕሮግራሞችን በመዘርጋት፣ ፖሊሲዎችን በመቅረጽና ፍትሀዊ የሀብት (በጀት) ክፍፍልን ማከናወን ዜጎች መብቶቻቸውን ይቀዳጃሉ ተብሎ ይገመታል። አለማቀፋዊ አሰራሮችም ደጋግመው እንዳረጋገጡት ልማት የሰው ልጆች መብት እንደሆነና ይህም

መብት ህዝቦች ለትምህርት፣ ለጤናና ለንጹህ መጠጥ ዉሃ ያላቸውን እድል የሚጠቁም ነው።

በዚህ ረገድ ነሀሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም የጸደቀው የኢፌድሪ ህገ-መንግስት ልማት የህዝቦች መብት መሆኑን ያረጋግጣል። ይህንን አስመልክቶም የህገመንግስቱ አንቀጽ 43 ንዑስ ቁጥር 1 "የኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሄሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው"ይላል።

የህግ መንግስቱ አንቀጽ 15 እንደሚያብራራውም "ማንኛውም ሰው በህይወት የመኖር መብት አለው" ሲል አስፍሯል። ይህም ሲባልም መንግስት በሰዎች መብት ዙሪያ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት መከላከል ተደርጎ መወሰድ ብቻ ሳይሆን መንግስት ለህብረተሰቡ ደህንነት ሲል የሚወስዳቸውን አዎንታዊ እርምጃዎችን ያካትታል።

ለምሳሌ፣

- የጤና አገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ፣
- የትምህርት ተቋማትን ማስፋፋት፣
- እንደ ንጹህ ውሃ የመሳሰሉ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በስፋት መዘርጋት

## 1.3. ሕገ-መንግስታዊ መሰረት

- ተጠያቂያዊ የአስተዳደር ስርዓትን ማስፈን

የመልካም አስተዳደር ስርአት መኖር ህብረተሰቡና ዜጎች በአከባቢያዊና በሀገሪቱ የሚያደርጉትን የተሟላ የልማት ተሳትፎ ህጋዊ መሰረት እንዲያዝ የሚያደርግ ነው። ይህም አሰራር የአንድ ዲሞክራሲያዊ መንግስት መገለጫ እንደሆነ ያረጋግጣል።

የመልካም አስተዳደር ጽንስ ሀሳብም በአንድ ሀገር ውስጥ ያለውን አገዛዝ ምንነት ከማሳየቱም በተጨማሪ የመንግስት ድርጅቶች፣ የንግድ ተቋማትና የሲቪል ማህበረሰብ አደረጃጀቶችን ቁልጭ አድርጎ የሚሳይ ስርአት ነው።

በተጨማሪም መልካም አስተዳደር ሲባል የወደፊቱን ጠቋሚ፣ ግልጽነት ያለው፣ የጠራ ፖሊሲን የሚከተል፣ ሙያተኞችን በውስጡ ያቀፈ፣ ከብልሹ ቢሮክራሲያዊ አሰራር የጸዳ፣ የመንግስት ተጠያቂነት የሰፈነበት እንዲሁም ጠንካራ የሲቪል ማህበራት ተሳትፎ የጎለበተበት እና ህጋዊ አሰራርን ተከትሎ የሚጓዝ ሂደት ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘም ተጠያቂነት፣ ግልጽነትና ሰፊ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ ድህነትን ለማስወገድ ቁልፍ ነገሮች በመሆናቸው ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰመርባቸው ይገባል።

የመልካም አስተዳደር ባህርያትና በኢፌድሪ ህገ መንግስት ውስጥ የተካተቱ አግባብነት ያላቸው የህግ አንቀጾች፦

| ባህሪያት | ጥቅሙ | በ1987 በኢፌድሪ ሕገ-መንግስት ውስጥ የተካተቱ አንቀጾች |
|---|---|---|
| ተሳትፎ | • መልካም አስተዳደር አሳታፊ በመሆኑ ዜጎች ሁሉ በፖለቲካዊ በኢኮኖሚያዊ ና በማህበራዊ ጉዳዮች ድምጻቸውን ባማሰማት ውሳኔ መስጠት መቻላቸው።<br>• ዜጎች በአስተዳደሩ ላይ ተጽእኖ ማሳረፍ መቻላቸውና የተሻለ ፖሊሲ ተቀርጾ እንዲተገበር ማስቻላቸው።<br>• አስተዳደሩም የዜጎችን ምኞትና ፍላጎት መረዳት መቻሉ።<br>• ተሳትፎአዊ መድረኮች የተለያዩ ፍላጎቶችን በማጣጣምና በማስታረቅ ወደ አጠቃላይ ፍላጎትና ግንዛቤ የሚያስገኙ መሆናቸው። | አንቀፅ 43/2/<br>ዜጎች በብሄራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው። |
| ግልጽነት | ግልጽነት የተገነባው በነጻ የመረጃ ፍሰት ላይ እንደመሆኑ በመንግስትና በሃላፊዎች የሚወሰኑ ውሳኔዎችም ሆኑ የሚፈጸሙ ድርጊቶች በህዝቡ ዘንድ ሊታወቁ ይገባል። ስለዚህም ግልፅነት ህዝቦች ስለመንግስት አሰራር እውቀት እንዲጨብጡ ማስቻሉ። | አንቀጽ 12(1)<br>ለህዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት |
| እኩልነት | ዜጎች ሁሉ በሃይማኖት፣ በዘር፣ በፆታ እንዲሁም በማህበራዊ ህይወት ሳቢያ አድሎ የማይፈጸምባቸውና እኩል መሆናቸው መረጋገጡ። | አንቀጽ 25<br>ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው። በመካከላቸውም ማንኛውም አይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል። |
| ተጠያቂነት | የህዝብ ተሿሚዎችና የሲቪል ሰርቪሱ አገልጋዮች ለሚደርሱበት ውሳኔና | |

| | | |
|---|---|---|
| | ለሚፈጽሙት ድርጊት ለህዝቡ ተጠያቂ መሆናቸውና የመንግስት ተሿሚዎችም (ባለስልጣናት) ህግንና የህዝቡን ጥቅምና ፍላጎት ተከትለው መስራታቸውን መቆጣጠር መቻሉ። | |

## 1.4. አሳታፊ የልማት አካሄድ፡-

ቀደም ሲል እነደተገለጸው የልማት ዓላማ ህዝብን ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን፣ ይህም ህዝብ የልማት ዓላማ ሳይሆን የልማት ባለቤት ነው። ምክንያቱም ህዝብ ምን እንደሚሻ፤ እንዴትስ እንደሚሰራው፤ መቼስ እንደሚያከናውነውና እንዴትስ አድርጎ እንደሚመራው ወሳኙ ራሱ ስለሆነ ነው።

የተሳትፎአዊ የልማት አካሄድ ዋና ትኩረትም ህብረተሰቡ ፈርጀ ብዙ በሆኑ የልማት ተግባራት ውስጥ ተሳታፊ ሆኖ ሲገኝ ነው። በዚህ አሳታፊ የልማት ተግባራት ውስጥ የሚካተቱ (የሚተገበሩ) ድርጊቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. ፍላጎትን ለይቶ ማወቅ፣
2. እቅድ ማውጣት፣
3. ውሳኔ መስጠት፣
4. ትግበራና ግምገማ ናቸው።

በመሆኑም አሳታፊ የልማት ዘዴ ማህበረሰቡ የውሳኔውና የድርጊቱ ባለቤት መሆኑን ያረጋግጣል።

ሌላው የአሳታፊያዊ የልማት አካሄድ ዋና ዓላማ የማህበረሰቡ ትክክለኛ ሁኔታ የሚጠናበት፣ የሚወሰደውም እርምጃ የሚታቀድበት ብሎም ውጤቱ የሚገመገምበት አካሄድ ነው።

## 1.5. ድህነትን ለማስወገድ ቀጣይነት ያለዉ የልማት እቅድ መዘርጋት፡-

ድህነትን ማስወገድ ዋናው የኢትዮጵያ መንግስት የልማት ዓላማ እንደሆነ ይታወቃል። ይህንንም ለማሳካት መንግስት የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ቀይሶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። የዚህ ስትራተጂ የመጀመሪያው ክፍልም እ.አ.አ ከ2002/03-2004/05 ተግባር ላይ ዉሏል። የተፋጠነና ቀጣይነት ያለው ድህነትን የማስወገድ የልማት እቅድ ሁለተኛው የድህነት ቅነሳ ስትራተጂ ፕሮግራም አካል ደግሞ እ.አ.አ ከ2005/06-2009/10 ስራ ላይ የሚውልና በኢኮኖሚውና በማህበራዊ ዘርፍ ውስጥ ያለውን የልማት ግብ ከማመላከት ባሻገር የህብረተሰቡና ሲቪል ማህበራት የድህነት ማስወገድ ተግባር ተሳትፎን ያበረታታል። የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ፕሮግራምም የመንግስት የልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች የስራ ሂደትን እንደገና የማዋቀር አሰራር (BPR) ስርዓት

የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአትን በመንግስት ድርጅቶች ውስጥ ለማሻሻል ሲባል የተዘረጋ ነው።

## 1.6. የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ፕሮጀክት (PBS) ከለላ ተፈጻሚነት፦

በዚህ መሰረታዊ አገልግሎት ከለላ ፕሮጀክት ዙሪያ በኢትዮጵያ መንግስትና በሌሎች ለጋሽ መንግስታትና ኤጀንሲዎች ስምምነቶች ተካሂደዋል። ፕሮጀክቱም የሚያተኩረው በአስተዳደር መሻሻል፤ በሰዎች የተሳትፎ ቁጥር መጨመርና እንደ ጤና፤ ትምህርትና የውሃ አቅርቦት በመሳሰሉ ክብካቤ በሚያስፈልጋቸው ወሳኝና መሰረታዊ አገልግሎቶች ላይ ነው።

ይህም ፕሮጀክት በዋነኝነት የሚያተኩረው ለመሰታዊ አገልግሎት አቅርቦት የሚደረገውን እንቅስቃሴና ለማህበራዊ ተጠያቂነት እድገት መጎልበት ነው። በዚህ በማህበራዊ ተጠያቂነት አሰራርም ዜጎች በመሰረታዊ አገልግሎቶች ዙሪያ ጥራት ያለው አስተማማኝና ቀልጣፋ አሰራር እንዲሰፍን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ከመሰል ዜጎች፤ ከመንግስት አካላትና ከህዝቡ አገልጋዮች ጋር የሚደራደሩበት አካሄድ ነው።

የመሰረታዊ አገልግሎት ከለላ አሰራር ዋና መነሻ ሀሳብ ያልተማከለ አገልግሎት አሰጣጥን ወደ ዝቅተኛው (ታችኛው) የወረዳ አስተዳደር የእርከን ደረጃ በማውረድና ወደ ህዝቡ በመቅረብም ጥሪትን (ሀብትን) አሰባስቦ የህዝቡን መሰረታዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች ለማሟላት ሲባል ነው።

አጠቃላይ የመሰረታዊ አገልግሎት ከለላ በኢትዮጵያ ውስጥ በ4 ክፍሎች የተዋቀረ ነው። እነሱም፦

1. ሀብትና ጥሪትን ወደ ክልልና ወረዳ በማውረድ የጤና፤ የትምህርት፤ የውሃ አቅርቦትና የግብርና ኤክስቴንሽን የምግብ ዋሶች አገልግሎትን የሚመለከት ነው።
2. አስፈላጊ የጤና ቁሳቁሶች በወቅቱ ተገዝተዉ ለተፈለገዉ አገልግሎት እንዲውሉ የገንዘብ አቅርቦትን የሚያመቻች ክፍል ነው።
3. ለአገልግሎቱ የሚመደበው በጀት ግልጽነት እና ተጠያቂነት ባለው መልኩ መከናወኑን የሚከታተል ነው።
4. በእቅድ አወጣጥና በበጀት ድልድል የሚሳተፉት ዜጎችና የሲቪል ማህበራት

ስለዚህም እነዚህ ከላይ የተገለጹት ክፍሎች (አካሎች) በመንግስታዊና በሲቪል ማህበሬት ድርጅቶች ውስጥ በስፋት በኢትዮጵያ በመተግበር ሂደት ላይ ያሉ ናቸው።

## 1.7. በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች አተገባበር፦

### የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች

- አስከፊ ድህነትንና ረሀብን ማስወገድ፣

- የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በአለም አቀፍ ደረጃ ከግብ ማድረስ፣
- የጾታ እኩልነት ማረጋገጥና ሴቶችን የማብቃት ስራን ማጠናከር፣
- የህጻናት ሞትን መቀነስ፣
- የእናቶች  ጤና ማሻሻል፣
- ኤች አይ ቪ/ኤድስን፤ ወባን እና ሌሎች በሽታዎችን መዋጋት፤
- በዘላቂነት የአካባቢ ጥበቃን ማረጋገጥ፤
- ለልማት ሁለንተናዊ አጋርነትን ማጎልበት፤

በኢትዮጵያ የሚሊንየሙ የልማት ግብ ከልማት ፖሊሲውና እቅድ ጋር በቅርብ የተጣመረ ነው። በአሁኑም ወቅት የሀገሪቱ አጠቃላይ የምርት እድገት (GDP) ፤ የመሰረተ ልማት ግንባታና የመሰረታዊ አገልግሎት እየተሻሻለ በመሄድ ላይ ይገኛል።

**ሁሉን አቀፍ አሳታፊ ስብሰባ**

- በፕሮጀክት ትግበራ የማህበረሰብ ተሳትፎ ጥቅም አብራራ/አስረዳ/
- በሁሉም መልኩ ማህበረሰቡን ያሳተፈ ፕሮጀክት ካለ በምሳሌ ግለጽ
- አንተ ባለህበት ወረዳ የመሰረታዊ አገልግሎት ከለላ አሰራር ምን ይመስላል?
- በ ”ድህነትን ለማስወገድ የተዘረጋው የተፋጠነ ቀጣይነት ያለው ልማታዊ ዕቅድ” በ “ሚሊኒየሙ የልማት ግቦች” እና በ “መሰረታዊ አገልግሎቶች  ፕሮጀክት” መካከል ያለውን ዝምድና ተገንዝበሀል? እንደምንስ የሲቪል ማህበራት ፕሮግራሞች

# 2. ማህበራዊ ተጠያቂነት፦

## 2.1. ዓላማ

የዚህ መመሪያ አላማ የማህበራዊ ተጠያቂነት ጽንስ ሀሳብና አሰራር እንዲሁም ክትትል ምን መሆን እንዳለበት የመግቢያ ሀሳብ የሚሰጥ ነው። ከዚህም በኋላም ተሳታፊዎች የሚከተለውን እንዲገነዘቡ ይጠበቃል።

- ማህበራዊ ተጠያቂነት ምን ማለት እንድሆነ?
- የማህበራዊ ተጠያቂነት ዘዴዎችንም የሚጠቀሙ እነማን እንደሆኑ ማብራራት፣
- የተለያዩ የማህበራዊ ተጠያቂነት ዘዴዎችንና አላማዎችን በሚገባ ተረድቶ ከማህበረሰብ ተሳትፎ ውጤት መመዝገቢያ ካርድ ጋር ማገናዘብ መቻል፤

## 2.2. ተጠያቂነት ማለት ምን ማለት ነው?

ተጠያቂነት ማለት ሃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎች ለሚወስዱት እርምጃና ለተሸከሙት ሀላፊነት ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚገደዱበት ስርአት ነው። ይህም የፖለቲካ፤ የገንዘብና የሃላፊነትም አቅም ያላቸው ሆነው በመንግስት አስተዳደር፤ በግል ተቋማት፤ በአለምአቀፍ የገንዘብ ድርጅቶችና በሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩትን ያጠቃልላል። ስለዚህ ተጠያቂነት በዜጎችና እነሱ በመረጧቸው ተወካዮች መካከል በዲሞክራሲያዊ ሂደት ውስጥ ድብቅ የሆነ ማህበራዊ ተጽእኖ ነው ማለት ይቻላል።

የዲሞክራሲ መሰረታዊ መርሆ እንደሚያስገነዝበው ዜጎች የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ሁሉ የህዝብ አገልጋዮችም የተጠየቁትን የመመለስ ግዴታ አለባቸው። ተመራጭ አካላትም ሆነ የሲቪል ሰርቪሱ አገልጋዮች ለሚፈጽሙት ተግባር ሁሉ ተጠያቂዎች ናቸው። በሌላ አነጋገርም ሃላፊነታቸውን አለአግባብ ሳይጠቀሙ የህዝቡን ፍላጎት ቀልጣፋና ዉጤታማ በሆነ መልኩ እንዲፈጽሙ የተጠያቂነት ህግ ያስገድዳቸዋል።

## 2.3. ማህበራዊ ተጠያቂነት ምንድን ነው?

ማህበራዊ ተጠያቂነት የአመራር ሂደትን፣ የአገልግሎት አሰጣጥ ውጤቶችን እና የሀብት አከፋፈል ውሳኔዎችን ማሻሻል ይረዳ ዘንድ ህዝባዊ፣ ግላዊና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ማገዝ ነው። ማህበራዊ ተጠያቂነት ዜጎች ድምጽ ከመስጠት ባሻገር በመንግስት፣ በሲቪል ማህበራት፣ በመገናኛ ብዙሃን እና በሌሎች የማህበረሰብ ተዋናዮች የሚወሰዱ እርምጃዎችን ተጠያቂነት አመላካች ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እና ስልቶችን ያካተተ ነው።

## 2.4. የማህበራዊ ተጠያቂነት ፋይዳዎች/ጠቀሜታዎች፦

በጥቅሉ ሲታይ ማህበራዊ ተጠያቂነት ከሌሎች ተግባራቱ ባሻገር መስተዳድርን፣ ህዝባዊ ፖሊሲዎችን እና አገልግሎቶችን፣ በአገልግሎት ተጠቃሚዎች እና አቅራቢዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል እና መንግስትም እውቀት /መረጃ/ አገዝ ውሳኔዎችን እንዲወስድ የሚያስችል ነው። ኣይነተኛ ጠቀሜታው በህጋዊ ፖለቲካዊ ተቋማት ስር የተደራጁ ማህበራዊ ቡድኖችን ማለትም ሴቶችን፣ ወጣቶችን እና ድሆችን በእምቅ ማህበራዊ ተጠያቂነት ተነሳሽነት ላይ አቅማቸውን እና ሀይላቸውን ማጎልበት ነው። በርካታ የማህበራዊ ተጠያቂነት መገልገያዎች /መሳሪያዎች/ ማለትም ያታዊ በጀት አመዳደብንና ተሳትፎአዊ ቁጥጥር ምዘናን የመሳሰሉትን በዋነኛነት መቀረፃቸው ኢ-እኩልነት ጉዳዮችን ለመቅረፍና አቅመ አናሳ ማህበራዊ ቡድኖች ሀሳባቸውን የመግለጽ፣ በምርጫቸው የማከናወን እና ተጠያቂነትን የማንሳት መብት እንዳላቸው ማረጋገጫ ለመስጠት ነው።

## 2.5. የክትትል ዘዴዎች

በርካታ የማህበራዊ ተጠያቂነት ዘዴዎች እና መተግበሪያዎች /tools/ አሉ። የእነኝህም ምርጫ መሰረት የሚያደርገው ክትትል በሚደረግበት ተግባር አይነት፣ በችግሩ ባህሪ

እና ስፋት፣ በፍላጎት እና አቅርቦት አቅም እና በማህበራዊ-ፖለቲካዊ መቸት /context/ ነው። ከፊሎቹ የማህበራዊ ተጠያቂነት ዘዴዎች የሚከተሉት ናቸው።

- አሳታፊ የበጀት አመዳደብና፣ ነፃ የበጀት ጥናት፣
- የገንዘብ አወጣጥ ዘገባ የበጀት አወጣጥ እና የግብአት ዘገባ፣
- የተሳትፎ ውጤት ክትትል፣ /የመከታተያ ዘዴዎች ሪፖርት ካርድ፣ ማህበራዊ ኦዲት እና የማህበረሰብ የውጤት መመዝገቢያ ካርድ ናቸው።/
- የዜጎች ዳኝነት ሰጪዎች /citizens juries/ ይፋ የአቤቱታ /የክስ/ መደመጥ፣ በህዝብ ሬድዮ፣ ግልጽ መተላለፊያዎች /መግቢያና መውጫዎች/ የዜጎች ቻርተሮች እና እንባ ጠባቂ ተቋም

## 2.6. የማህበራዊ ተጠያቂነት አንኳር ነጥቦች፡-

ማህበራዊ ተጠያቂነት ሰፊና በርካታ የተግባር ክትትል የሚያካትት ሲሆን ለአብዛኞዎቹ ማህበራዊ ተጠያቂነት አቀራረቦች የወል የሆኑ በርካታ ነጥቦች አሉት። እነሱም (i) የመረጃ ተደራሽነት (ii) የዜጎች ድምጽ ተሰሚ እንዲሆን ማስቻል እና (iii) ለለውጥ በሚደረገው የድርድር ሂደት ተሳታፊነት ናቸው።

- መረጃ ተደራሽነት ወይም ጭብጥነት እና ይፋነት የማህበራዊ ተጠያቂነት ወሳኝ ገጽታዎች ናቸው። ባለስልጣናትን ተጠያቂ የሚያደርግ አስተማማኝ መረጃን ማጎልበት ይበልጡኑ የሚያካትተው ከመንግስት እና አገልግሎት አቅራቢዎች የመረጃ አቅርቦትን እና ከመንግስት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከማህበረሰቦች እና ከዜጎች ደግሞ የመረጃ ፍላጎት ነው። የመንግስት ግልፅነት፣ ዳታንና ዶክመንቶችን (ሪፖርቶችን) የማቅረብ አቅም፣ የፖሊሲ ጭብጦች፣ የበጀት አፈ.ቃቀድ እና መረጃዎች፣ የግብአቶች፣ የውጤቶች (outputs) የወጪ መጠን መዘርዘር እንዲሁም የኦዲት ግኝት መሰል የመረጃ አቅርቦቶች ተደራሽ እንዲሆኑ ለማስቻል እጅግ ወሳኝ ናቸው። የማህበራዊ ተጠያቂነት ጣልቃገብነት የመነሻ ትኩረት ለላቀ መረጃን የማግኘት መብት እና ህዝባዊ ግልጽነት ማሳመንን (መገፋፋትን) ይመለከታል። መረጃን የማግኘት ፍላጎት በርካታ አሳታፊ ዘዴዎችን እና መገልገያዎችን ማላትም የዜጎች ሪፖርት ካርዶች፣ የማህበረሰብ ውጤት መመዝገቢያ ካርዶች እና አሳታፊ የክትትል እና ምዘና ዘዴዎችን በመቅረጽ ዳታን ለማግኘት እና በተመሳሳይ መልኩም ንቃተ-ህሊናን ለማበልጸግ እና በክልል ደረጃ ማስተባበርንና ማደራጀትን መቻል ነው።
- ሌላው የማህበራዊ ተጠያቂነት ቁልፍ ጉዳይ የዜጎች ጥያቄዎች (ፍላጎቶች)፣ አስተያየቶች እና አሳሳቢ ጉዳዮች እንዲመጡ ማስቻል፣ መንግስት የዜጎች ተቀዳሚ ፍላጎቶችን እንዲገነዘብ እና በተሻለ መንገድ ዜጎቹን ማገልገል ይችል ዘንድ ማገዝ ነው። የዜጎች ድምጽ መሰማትን ለማጠናከር የተቀየሰው ዋንኛ ስትራተጂ የህዝባዊ ውይይት፣ በዜጐች እና በመንግስት የክርክር መድረኮችን መፍጠር፣ የዜጎች በራስ የመተማመንና የመብት ግንዛቤአቸዉን ከፍ ማድረግ ነው። እንዲሁም በተባበረ ጠንካራ ድምጽ ሃሳብ የሚገለጽበት የጥምረት እና ትብብር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ብሎም ዘመናዊ እና ባህላዊ የሚዲያ አይነቶችን ማጎልበት የሚያስችል ስትራተጂም ያካትታል። ለማህበራዊ ተጠያቂነት ተነሳሽነት ዋንኛው ፈታኝ ነገር ይበልጥኑ ደሀዎችን እና

የተገለሉትን ቡድኖች ድምጽ አለመታፈኑን ወይንም በሌላ ይበልጥ ሀያል እና ተስማሚ ቡድኖች ተጽዕኖ ስር አለመውደቃቸውን ማረጋገጥ ነው።

- በዜጎች እና በመንግስት መካከል ፊት ለፊት ግንኙነት ማድረግ ይችላሉ። ለምሳሌ በማህበረሰብ ደረጃ ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ቀጥታ መገናኘት አሊያም በተዘዋዋሪ የምክክር እና ድርድር መንገድ ማስታረቅን ሊሆን ይችላል። በድርድር ለውጥ ዜጎች ቡድኖች ሁለቱንም ማለትም ተለምዶአዊ (formal) ወይንም ኢ-ተለምዶአዊ (informal) የማሳመኛ መንገድ፤ ግፊትን፤ ሽልማትን እና እቀባትን (reward & sanction) ሊጠቀሙ ይችላሉ። እነኚህም ህዝባዊ ግፊት መፍጠርን ያካትታሉ። ለምሳሌ ህዝባዊ ስብሰባ ይበልጥ ጠቃሚነቱ ለአብዛኛው የማህበራዊ ተጠያቂነት አቀራረቦች ተለምዶአዊ የሆኑት አንኳር ጉዳዮች የሚያካትቱት የመረጃ ተደራሽ ማድረግን፣ የዜጎች ድምጽ እንዲሰማ ማስቻልን እና በለውጣዊ የድርድር ሂደት ተሳታፊነት ነው።

## 2.7. ማህበራዊ ተጠያቂነትን ለማስፈን ወሳኝ ምክንያቶች (መንስኤዎች)፦

ውጤታማ የማህበራዊ ተጠያቂነት የሚወስነው በወሳኝ መንስኤዎች (ምክንያቶች) መገኘት ሳቢያ ነው። እነሱም፦

- በዜጎችና መንግስት መካከል ያለውን ርቀት ማጥበብ፣
- የዜጎች እና ሲቪል ማህበራት ተዋናዮች አመለካከት እና አቅም ማሳደግ፣
- የክልል (አከባቢያዊ) መንግስት ተዋናዮች አመለካከት እና አቅም ማጠናከር፣
- ምቹ ሁኔታ መፍጠር ናቸው።

በቡድን ውስጥ የተካተቱት እያንዳንዳቸው መንስኤዎች /ምክንያቶች/ በሶስቱ የማህበራዊ ተጠያቂነት አንኳር ነጥቦች አኳያ ሊቃኙ ይችላሉ። የማህበራዊ ተጠያቂነት ተነሳሽነት ብዙውን ጊዜ ተጠያቂነትን ማጎልበት የሚያስችሉ ስልቶችን በመፍጠር ወይንም በማጠናከር ነው። በእነኚህ አራት ቁልፍ ጉዳዮች ዙሪያ ያሉትን ችግሮች በመፍታት ማህበራዊ ተጠያቂነትን ማገዝ የሚችሉትን የመንግስት የሲቭል ማህበረሰብ፤ የልማት አጋሮች ወይንም የሌሎች ተዋናዮች ድርጊቶችን ከግንዛቤ መክተት ጠቃሚ ነው። የማህበራዊ ተጠያቂነት ስልቶች ውጤታማ (ስኬታማ) እንዲሆን ለማስቻል የሚያስፈልጋቸው ነገር ቢኖር የዜጎችን ፈቃደኝነት እና አቅም በሚያጎላብቱ ጥረቶች እና ይበልጥ ምቹ ሁኔታን በሚፈጥሩ የሲቪል ማህበራት እና የመንግስት ተዋንያን እንቅስቃሴ መታገዝን ነው።

## ውይይት እና ትኩረት እሳቤ

- በማህበራዊ ተጠያቂነት መገልገያዎች መተግበር ተጠቃሚው ማነው?
- ከላይ የተሰጠውን የማህበራዊ ተጠያቂነት ትርጉም አንብብና የተግባራዊነቱ አድማስ አገናዝብ፤
- ከላይ የተሰጠዉን ትርጉም ውስን ነው ብለህ ታስባለህ? ከሆነ ለምን? ካልሆነስ? ኋላፊዎች ተጠያቂነታቸው ለማን ነው?
- የበታች እና በላይ ተጠያቂነት የሚለውን ሀሳብ ማብራራት ትችላለህ? አዎን ከሆነ አስረዳ፤
- አገልግሎት አቅራቢ ማነው?

- በማህበረሰብ ተሳትፎ ውጤት መመዝገቢያ ካርድ ሂደት ስራ ላይ የዋለው መገልገያ ምንድን ነው?
- አይነተኛ የማህበራዊ ተጠያቂነት ዘዴ አመራረጥን የሚወስነው ምንድን ነው?

# 3. የማሕበረሰብ የአገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደቶች፡-

ይህ መመሪያ የሚያተኩረው ጠቃሚ የሆነውን የስልጠናውን አካል ነው። ምክንያቱም የማህበረሰብ የአገልግሎት መመዘኛ ካርድ ዘዴን በመጠቀም ማህበራዊ ተጠያቂነትን ማከናወኛ ተግባራዊ ገጽታውን ስለሚዳስስ ነው። ስለሆነም የዚህ መመሪያ አላማ ተሳታፊዎች በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ  የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ እንዲተገበሩ ለማስቻል ነው። ይኸው መመሪያ ሲጠናቀቅ ተሳታፊዎች የሚከተሉትን መከወን ይችላሉ።

- በማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደቶች ያሉትን የተለያዩ ደረጃዎችን ይለያሉ፣
- በየደረጃው የሚወሰዱትን እርምጃዎችን ይለያሉ፣
- በእያንዳንዱ ደረጃ እና እርምጃ ውስጥ ያሉትን መሰረታዊ ህቆችን ይገነዘባሉ፣
- የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ዘዴን መጠቀም የማህበራዊ ተጠያቂነት ክትትል ተግባር ያከናውናሉ።

## 3.1. ትርጓሜ (ትርጉም)፡-

የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ከበርካታ የማህበራዊ ተጠያቂነት የክትትል ዘዴዎች አንዱ ነው። የማህበራዊ ኦዲት እና የሥነ ዜጋ ሪፖርት ካርድ (CAC) ድብልቅ (hybrid) ነው። አገልግሎት አቅራቢዎችን ከማህበረሰቡ ጋር በማጣመር ማህበራዊ እና ህዝባዊ ተጠያቂነትን በእርግጠኝነት ያስጨብጣል። ስለሆነም ዜጎች ከአገልግሎት አቅራቢዎች ፈጣን ምላሽ ማግኘት ይችሉ ዘንድ ስልጣን (አቅም) ይኖራቸዋል።

በዚሁ መነሻ የማህበረሰብ ተሳትፎ ውጤት መመዝገቢያ ካርድ ጠቃሚ ነጥቦችን ነቅሶ ማውጣት ይቻላል። እነሱም፡-

- የማህበራዊ ተጠያቂነት የመከታተያ ዘዴዎች አንዱ ነው፣
- የአገልግሎት ተጠቃሚዎችና አገልግሎት አቅራቢዎች ማለፊያ የግንኙነት ዘዴ ነው፣
- የመልካም አስተዳደር መገለጫ የሆኑንት በርካታ ባህርያትን ያካትታል፣
- ዜጎች በራሳቸው ጉዳይ ተመልካቾች ሳይሆኑ ወሳኞች እንዲሆኑ አቅም (ስልጣንን) ያጎናጽፋል፣
- የወል ተጠያቂነትን መርህ መሰረት ያደረገ ነው።

## 3.2. ዓላማ ግብ እና ስትራተጂ

ዓላማ፡-

የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ አላማ የአገልግሎት አሰጣጥ እና የማህበራዊ ስራዎች ጥራት ተደራሽነት እና ጠቀሜታ ሲሆን ይህም የአገለግሎት አቅርቦትን ማጎልበት እና ማሳደግ ነው።

ግብ፡-

የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደት የመጨረሻ ግብ አገልግሎት አቅራቢዎች ተጠያቂነታቸውን ለህዝብ በማድረግ በየደረጃው የተሻሻለ የአገልግሎት አቅርቦትን መሻት ነው።

## ስትራቴጂ /ስልት/፡-

ስትራቴጂ ሁለቱንም ማለትም አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና አገልግሎት አቅራቢዎች የሚሳተፉበት የውይይት መድረክን መጠቀም ነው።

## 3.3. መሰረታዊ ባህርያት፡-

እጅግ የተለመዱት (የታወቁት) ባህርያት የሚከተሉት ናቸው

- የሚከናወነው በዝቅተኛ ደረጃ ሲሆን ማህበረሰቡን እንደ አንድ የጥናት አካል ይጠቀምበታል፣
- በትኩረት ቡድኖች ውይይት ሳቢያ መረጃዎች ይሰባሰባሉ፣
- ለአገልግሎት አቅራቢዎች ፈጣን ምላሽን ያስጨብጣል፣
- ለፈጣን ምላሽ እና ለውሳኔ ሰጭነት አጽንኦት ይሰጣል፣
- በተጠቃሚዎች እና አገልግሎት አቅራቢዎች መካከል የጋራ ውይይት፣ ማሻሻያ እቅዶች መንደፍና ክትትሉም ቀጣይነት እንዲኖረው ያስችላል።

## 3.4. የአገልግሎት መመዘኛ ካርዱ ጠቀሜታዎች፡-

ካርዱ ለአገልግሎት አቅራቢዎች እና ተጠቃሚዎች የሚሰጠው ጥቅሞች፡-

ሀ/ ለአገልግሎት ተጠቃሚዎች ስለስራ አፈጻጸማቸው የአገልግሎት ሰጪዎች ገንቢ ምላሽን ለመስጠት፣

ለ/ ለአገልግሎት አቅራቢዎች ስለ አገልግሎቶቻቸው እና ፕሮግራሞቻቸው አካሄድ አዎንታዊነትና አሉታዊነት ከማህበረሰቡ በቀጥታ ለማወቅ ያስችላቸዋል። ከዛም በተጨማሪም ለዜጎች መብቶች፣ ፍላጎቶችና ምርጫዎች ምላሽ መስጠት የሚያስችል እውቀት፣ ውሳኔ እና የፖሊሲ ምርጫ ለማድረግ ማገዝ ዋንኞቹ ናቸው።

## ዝርዝር ጠቀሜታዎች፡-

- በአገልግሎት ሰጪዎች እና ተጠቃሚዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ያሻሽላል፣

- አገልግሎት አቅራቢዎች ለተጠቃሚዎች ያለባቸውን ተጠያቂነት፣ ግልጽነት እና ሃላፊነትን ያዳብራል፣
- ለሚከሰቱ ችግሮች እና ለመፍትሄዎቻቸው የጋራ ግንዛቤን እንዲፈጥሩ ያግዛል፣
- በተለያዩ የማህበረሰቡ ዝንባሌዎች (ፍላጎቶች) የጋራ ስምምነት መፍጠሪያ መድረክነት ያገለግላል፣
- የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች የፕሮጀክት ባለቤት አካል እንዲሆኑና እንዲሰማቸው እድል ይፈጥርላቸዋል፣
- የአገልግሎት ሰጪዎች እና ተጠቃሚዎች ሚናና ሀላፊነቶችን ያብራራል፣
- የማህበረሰብ ተሳትፎን በማበረታታት በአገልግሎት አቅራቢዎች እና ተጠቃሚዎች መካከል ገንቢ ውይይት የማካሄድ ባህል እንዲዳብር ያስችላል፣
- ሙሰኛ ባለስልጣናትን ማጋለጥ ያስችላል፣
- አገልግሎት አቅራቢዎች ለተጠቃሚዎች እንዴት ተጠያቂና ሃላፊነት ወሳጅ እንደሚሆኑ ማየት ያስችላቸዋል፣
- ከማህበረሰቡ ጋር እንዴት በመሆን አገልግሎት ሰጪዎች እድገታቸዉና የአገልግሎት ጥራታቸዉን ለመከታተል ያግዛቸዋል፣
- ለተሻሻለ የአገልግሎት አቀራረብ የበኩላቸውን እገዛ ማድረግ የሚችሉትን የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ባህሪ ለማሻሻል የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል፣
- የበጀት አጠቃቀም እና ተጠያቂነትን ያጎለብታል።

## 3.5. የአገልግሎት መመዘኛ ካርድ ፈታኝ ጉዳዮች፡-

በህዝባዊ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ክንዋኔዎች ላይ ማህበረሰቡ በተለይም በዘልማድ ለሚንቀሳቀስ የቢሮክራሲያዊ አስተዳደር ስርአት የማህበራዊ ተጠያቂነት የክትትል ስልት ስራ ላይ ማዋል አዲስ ነገር ነው።

በዚህ ረገድ አዳዲስ ህሳቤዎችን እና የአሠራር ዘዴዎችን ለማህበረሰቡ የአገልግሎት መመዘኛ ካርድ አማካይነት ማስተዋወቅ ችግሮች እንደሚያጋጥሙ ማሰብ ያስፈልጋል። ከሚጠበቁት ችግሮች የተወሰኑት የሚከተሉትን ይመስላሉ።

- መቀበል ጊዜ ይወስዳል ሆኖም በመጀመሪያ ላይ ቀላል እና ያልከበደ ሥራ ሊሆን ይችላል።
- ጥሩ የማስተባበር ክህሎት ከሚጠበቁት ነገሮች ውስጥ አንዱ ሲሆን ይህ በደንብ ካልተያዘ ወደ ግጭት ሊያመራ ይችላል።
- አንዳንድ ጊዜ ክንዉኖችን ከመቆጣጠር አንፃር ግለሰቦች ሊመረጡ ወይም ኢላማ ሊሆኑ ይችላሉ።
- ማስተባበሩ በጥሩ ሁኔታ ካልተሰራ በአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ዘንድ የሚጠበቁትን ውጤቶች ሊያሳንስ ይችላል።

በአጠቃላይ በፍላጎት እና በአገልግሎት ሰጪዎች ችሎታ መካከል መመጣጠን እንዲኖር ያስፈልጋል።

## 3.6. የአገልግሎት መመዘኛ ካርድ ውጤታማ የአፈፃፀም መስፈርቶች፡-

የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ውጤታማ አፈፃፀም የሚከተሉትን ታሳቢዎች ያደርጋል፡-

- የአካባቢውን አስተዳደራዊ መዋቅር በደንብ ማወቅ፤
- አሳታፊ የሆነ የማስተባበር ጥሩ ክህሎት፤
- የአገልግሎት ተጠቃሚዎች፣ አቅራቢዎች እና የሌሎች የአካባቢው ባለድርሻ አካላትን ከፍተኛውን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚያስችል ጠንካራ ሁኔታዎችን በፍጥነት የመገንዘብ እንቅስቃሴዎች፤
- በደንብ የታቀደ የማህበረሰብ የውጤት መመዝገቢያ ካርድ ሂደት

**የተሟላ /የካርድ ልምምድ**
በወረዳዎ ውስጥ የማህበረሰቡ የውጤት መመዝገቢያ ካርድ ለመፈፀም ሊኖሩ የሚችሉ ችግሮች እና መልካም አጋጣሚዎች

# 4. የማስተባበር ክህሎት /ችሎታ፡-

## 4.1. ዓላማ፡-

- የአስተባባሪውን ሚና እና ኋላፊነት ለመግለፅ፣
- የማስተባበር ክህሎት /ችሎታ/ እና ብቃት ለማጎልበት፤
- ተጠቃሚዎችን እና አገልግሎት አቅራቢዎችን ለመርዳት፤

## 4.2. ትርጓሜ እና ሚና፡-

አስተባባሪው የቡድን ሂደትን መምራት፣ የቡድን ስብሰባዎችን ዋና ነጥብ መገንባት እና ስብሰባዎቹን መዳኘት ሲሆን ይህም መሰረታዊ ፍልስፍና እያንዳንዱ ግለሰብ ለሌሎች አባላት ሊያካፍለው የሚችለው ልምድ እና እውቀት አለው የሚል እምነት ነው። በመሆኑም የአስተባባሪው ሚና የሚከተሉት ይሆናሉ።

- መርሐ ግብርን መንደፍ /የእለት መርሐ ግብር፣ ቴክኒኮች መምረጥ ወዘተ/
- አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች እና ማቴርያሎች ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- የራሱን/የራሷን አስተዋፅኦ በማክበር ስብሰባውን መምራት፣
- ሌሎች እውቀታቸውን እና ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ማድረግ፣
- የመማሪያ ሂደት እንዲኖር ማስቻልና፣ የሚፈለገው ውጤት መገኘቱን ማረጋገጥ፣

## 4.3. የማስተባበር ብቃት እና ዘዴዎች፡-

i/ ብቃት

ስብሰባው በተለይም ስልጠና ወይም ወርክሾፕ በሚሆንበት ጊዜ አስተባባሪዎቹ በውይይቱ ጉዳይ ላይ በቂ እውቀት ያላቸው መሆን አለባቸው። ሆኖም አስተባባሪው/ዋ የራሱን/ሷን አመለካከት መጫን የሌለባቸው ሲሆን በተቃራኒው ተሳታፊዎቹ ሃሳባቸውን እንዲያወጡ/እንዲያጎለብቱ መፍቀድ አለባቸው። ሆኖም አስተባባሪዎች የጉዳዩ ሰዎች መሆናቸውን ቀሪ አያደርገውም።

## ii/ የአካሄድ ዘዴዎች

አስተባባሪዎቹ ለተሳታፊዎች የሚከተሉትን ዘዴዎች መንደፍ አለባቸ፡-

- ሃሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ/እንዲያብራሩ ነጥቦቹ ላይ እንዲያተኩሩ፤
- ዘና እንዲሉ እና ጭንቀት እንዲያስወግዱ፤
- የእኩልነት ስሜት እንዲሰማቸው፤
- የተደረገውን ውሳኔ እንዲያስታውሱ፤

## iii/ አስተባባሪዎቹ የሚከተሉትን መቻል አለባቸው፤

- በተሳታፊዎች መካከል ጥሩ ግንኙነት እንዲኖሩ ማበረታታት፤
- ግለሰቦች የሚሰማቸውን እንዲገልፁ ተገቢውን ማድረግ፤
- በተሳታፊዎች መካከል እንዲሁም ከእርሱ/እርሷ ጋርም የእኩልነት ድባብ እንዲኖር መፍቀድ፤
- በተሳታፊዎች መካከል የመተማመን መንፈስ ለመፍጠር መሞከር፤

## 4.4. ሶስቱ የሰስተባባሪዎች መለያዎች

ሀ. እነዚህ አስተባባሪዎች ሚናቸውን የጉዳዩ ኤክስፐርት፣ የመማር ማስተማር ዳይሬክተሮች፣ በሁኔታው ውስጥ ያለውን ስልጣን እንደያዙ አስታራቂዎች እና ገምጋሚዎች አድርገው ያዩታል። እንዲህ ዓይነቶቹ አስተባባሪዎች በሚከተሉት ላይ ያዘነብላሉ፤ መልሶችን ይሰጣሉ፤ የትምህርት ዓይነት ሌክቸር እና ማብራሪያ ያቀርባሉ፤ ግቦችን ያስቀምጣሉ፣ ውሳኔ ይሰጣሉ፣ መረጃ ያስተላልፋሉ፣ በቀዳሚነት ከአስተባባሪዎች ለመማር እና ሃሳቦችን ለማግኘት የሚጠብቁ ሲሆን ከሌሎች ተሳታፊዎች የሚገኙ ግብዓቶች ላይ ብዙም አያግዳቸውም።

ለ. እነዚህ አሰተባባሪዎች የስብሰባዎቹን ዓላማዎች ቀርፀው የሚያስቀምጡት ከተሳታፊዎች ጋር በጋራ በመሆነ ነው። የመነሻ ቅርፅ ያቀርባሉ፤ ዓላማዎችን በመወሰን ላይ ተሳታፊዎችን ያሳትፋሉ፣ ዉሳኔ ለመወሰን ከተሳታፊዎች ጋር ይተባበራሉ፣ ውሳኔዎችን ያመቻቻሉ፣ ጥያቄዎችን፣ መልሶችን እና መፍትሔዎችን ያሳውቃሉ፣ ስለ ጉዳዩ መረጃ ይሰጣሉ፣ ተሳታፊዎች የራሳቸው መፍትሄዎች እንዲፈልጉ ያዳምጧቸዋል።

ሐ. እነዚህ አስተባባሪዎች ተቀዳሚ ሚናቸው መማርን ወይም ችግር መፍታትን እንደ ማስተባበር አድርገው ያዩታል። እንደ አማካሪ እና አሰልጣኞች ይንቀሳቀሳሉ። ራሳቸውን እንደ አቀጣጣይ ያያሉ፣ ተሳታፊዎች ፍላጎታቸውን እንዲዳስሱ፣ ጥያቄዎች እንዲጠይቁ፣ አስተያየቶች እንዲሰጡ ያበረታታሉ፣ የሚፈልጉትን ሀሳቦች እንዲለዩ ይረዷቸዋል ምልከታዎችን ይካፈላሉ፣ ያዳምጣሉ፣ ያሰለጥናሉ።

## 4.5. የጥሩ አስተባባሪዎች መለያ ብቃቶች

- በሌሎች ሰዎች እና በብቃታቸው ላይ እምነት አላቸው፤
- ትዕግስትና እና ጥሩ የማድመጥ ችሎታ አላቸው፤
- አዳዲስ ክህሎቶችን ለመማር ራሳቸውን የሚያውቁ እና ግልጽ ናቸው
- ትዕቢት የሌለበት በራስ መተማመን፤
- የሌሎችን አመለካከት ማክበር እና ሃሳቦቻቸውን በሌሎች ላይ አለመጫን፤
- በተሳታፊዎች መካከል በራስ የመተማመን እና የእኩልነት ድባብ የመፍጠር ችሎታ/ብቃት፤
- ዘዴዎችን እና ቅደም ተከተሎችን ለመቀየር ያላቸው የመለዋወጥ ችሎታ እና ባሉ ዘዴዎች ቅደም ተከተል ላይ ሁሌም ግትር አለመሆን፤
- የቡድኑን ስሜት በቶሎ የመገንዘብ ችሎታ እና ወዲያውኑ በቦታው ዘዴዎችን የመቀየር ወይም መርሀ ግብርን የማስተካከል ችሎታ፤
- ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አቅጣጫዎችን ማሳየት፣ ማለትም ተሳታፊዎች እንዲሳተፉ እና የራሳቸው የሆነ የአቀራረብ ዘዴ እንዲያቀርቡ መፍቀድ

- ይህን ይወቁ፦ የምንማረው፣
  - 1% በመቅመስ
  - 2% በመዳሰስ
  - 3% በማሽተት
  - 11% በመስማት
  - 83% በማየት

- ይህን ይወቁ፦ የምናስታውሰው፣
  - ካነበብነው ውስጥ 10 በመቶ
  - ከሰማነው ውስጥ 20 በመቶ
  - ከየነው ውስጥ 30 በመቶ
  - ካየነው እና ከሰማነው ውስጥ 50 በመቶ
  - ከተናገርነው ውስጥ 80 በመቶ
  - ከተናገርነው እና ከሰራነው ውስጥ 90 በመቶ

ስለዚህ በማናቸውም የቡድን ስብሰባዎች ውስጥ በእይታ ተደግፎ የሚቀርብ ነገር እና አሳታፊ ዘዴዎች በጣም ውጤታማ ናቸው።

## ከስበሰባ በፊት

- ለስብሰባው የሚቀርቡት ሰነዶች ምን እንደሆኑ ይወቁ። በጥንቃቄ ይመልከቷቸውና ትኩረት ያገኙትን እውነታዎች እና ጉዳዮች ማስታወሻ ይውሰዱ፤

- ስብሰባው ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ሊያስኬድ የሚችል ጥያቄ ያዘጋጁ፣ ጥያቄዎቹን መቅረፅ ክህሎቶች/ችሎታ እንደሚጠይቅ ያስታውሱ፤
- ለስብሰባው አስደሳች የሆነ ነገር ያዘጋጁ፣ ስኬታማ እንዲሆን የተሳታፊዎቹን ስብሰባ ይወቁ፣
- ስብሰባውን እነደ አመቺነቱ ይለዩና ለእያንዳንዳቸውም ጊዜ ይሰጡ፣
- በስብሰባው ቦታ ቀደም ብለው በመሄድ ሁሉም ነገር ዝግጁ መሆኑን ያረጋግጡ /ማቴርያሎች፣ የመቀመጫ አደራደሮች፣ መሳሪያዎች ወዘተ… በአግባቡ መዘገጃጀታቸውን/
- ስብሰባውን በጥሩ ለዛ እና በሙሉ ትጋት ይጀምሩ።

## በስብሰባው መጀመሪያ ላይ

- ስብሰባውን በሰዓቱ ይጀምሩ፣ መግቢያ/ማስታወቂያ ያድርጉ፣ ተሳታፊዎች እርስ በርሳቸው የሚተዋወቁ ከሆነ ራሳቸውን እንዲያስተዋውቁ ያድርጉ፣ ስብሰባው የተያዘለትን ፕሮግራም ሳይለቅ ፈጠራ በተሞላበት አኳኋን ይምሩ፤
- ጉዳዩን፣ ዓላማዎቹን፣ የጊዜ መርሐ ግብር፣ ዘዴዎቹ፣ ደንቦች እና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን ያስተዋውቁ፣
- ውይይቱን የሚጀምር ይመድቡ፣ ሪፖርት የሚፅፍም ይሰይሙ።

## ስብሰባው/ውይይቱ በሚካሄድበት ወቅት፤

- ስብሰባው በጓደኝነት መንፈስ እና ዘና ባለ ድባብ እየተካሄደ መሆኑን ይከታተሉ፣ አላስፈላጊ ክርክርን ያስወግዱ፤
- እያንዳንዱ ተሳታፊ በተራው መናገሩን ያረጋግጡ፣ የተወሰኑት የሚያፍሩ ከሆነ እንዲናገሩ ያደፋፍሯቸው፣ ጊዜ የሚያባክነውን እና ከርዕሱ ዉጭ የሆነውን በትህትና ይገድቡት/ያስቁሙት፤
- የውይይቱን ቁልፍ ቃላት ለመፃፍ ፍሊፕ ቻርቶችን፣ ካርዶችን ወይም ነጭ ሰሌዳዎችን ይጠቀሙ፤
- ለጥያቄዎች/ትችቶች ረጅም ማብራሪያ በመስጠት አይመልሱ፣ ጥያቄዎችን ተሳታፊዎች እንዲመልሷቸው ወደ እነርሱ ይመልሷቸው/ይስጧቸው፤
- ተናጋሪዎች ነጥቦቹን መያዛቸውን እና ከጭብጡ አለመውጣታቸው ያረጋግጡ፣ ውይይቱ ወደ ክርክራዊ ምልልስ እንዳይቀየር ያድርጉ፤
- ?
- እንደሁኔታው ግትር አይሁኑ ሆኖም ከጊዜ ሰለዴው በጣምም አይራቁ፣
- ከቡድኑ ጋር ክርክር አያድርጉ፣ ማድረግ ያለበዎት እንደ አገናኝ እንጂ ባላንጣ አይደለም፤
- ከደከመዎት ጉልበት የሚሰጥዎትን አድርጉ፣ ከሰለችዎት ዘዴ ይቀይሩ፣ የተወሰኑ ጥያቄዎች ያቅርቡ፤
- ቡድኑ እየተወጣጠረ እና አስፈሪ እየሆነ ከመጣ እየተከሰተ ያለውን በመጠቆመ አስተያየቶችን ይጠብቁ፣ የራስዎን ሃሳብ እንዳይጭኑ ጥንቃቄ ያድርጉ፤
- ማንንም እንዳያስቀድሙ ይጠንቀቁ፣ በሚሰጡበትም ጊዜ ለይተው ለማወቅ ይሞክሩ፤

- በቡድን ውስጥ ጓደኛዊ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ያበረታቱ፣ አብረዋቸው በሚቆዩበት ጊዜ ግልፅ እና ሰላማዊ የውይይት አካሄዶችን ለመማር ለማስተማር ይሞክሩ፤
- በጣም የበዛ ጣልቃ ገብነት የቡድኑን በራስ መተማመን እንደሚሸረሽር ጥቂት የሆነ ጣልቃ ገብነት ግን ያለዉን አቅጣጫ እና ጉዳዩን ሙሉ ለሙሉ ከመመርመር ሊገታ እንደሚችል ያስታውሱ።

## ስብሰባው ከማለቁ በፊት

- የተባለዉን ነገር መዝግበው ይያዙ፤
- አንድ ነገር መደረግ ካለበት ማን? ምን? እና መቼ? መስራት እንዳለበት ይመልከቱ፤
- ለተሳታፊዎች የዕለቱ ውይይት ከመጠናቀቁ በፊት ምን እንደተሰማቸው እንዲገልጹ ዕድል ይስጧቸው።

## 4.6. ማህበረሰብ እና ህዝብን በማስተባበር ረገድ ተጨማሪ ነጥቦች፡-

### – የአገልግሎት አቅራቢዎችን በተመለከተ

- ዓላማውን ማብራራት፣ ደንቦቹን መከተል እና ግንኙነቶችን መገንባት፤
- እያንዳንዱ ተሳታፊ በሀብትነት የሚታይ ሰው መሆኑን መግለጽ፤
- እስካሁን ለተከናወኑት ጥረቶቻቸውን ማድነቅ፤
- አከራካሪ ዕይታዎችን አግባበነት ባለው ሰው፣ ቡድኖች ጊዜ፣ ጋር የሚታዩ ወይም የሚፈቱ መሆናቸውን መግለጽ፤
- መረጃውን ለአገልግሎት አቅራቢዎች በሁሉም ደረጃዎች ላይ ያካፍሉ፤
- ትክክለኛውን አጀንዳ ለአገልግሎት አቅራቢዎች ያቅርቡ።

### – ማህበረሰብን በተመለከተ

- ሥራዎቹን እና ዓላማውን በግልጽ፣ በዝርዝር ማብራራት፣ ተሰታፊው ሥራዎቹን እና ውጤቱን መረዳቱን ማረጋገጥ፤
- ሁልጊዜም ማህበረሰቡ ከየትኛውም ሌላ ሰው የበለጠ ስለ አገልግሎቱ የሥራ አፈፃፀም ችግር እና መፍትሄውን እንደሚያውቅ መረዳት፤
- እስከአሁን የተከናወኑትን የማህበረሰብ አስተዋፅኦዎች ማድነቅ፤
- ስብሰባዎችን እና ውይይቶችን በፍላጎታቸው ላይ ተመስርቶ ማዘጋጀት
- የተለያዩ የማህበረሰብ ቡድኖችን ተሳትፎ ማበረታታት፤
- በጣም ደሃዎች የበለጠ ድምፅ እንዲሰጡ እድሉን መስጠት፤

**የብድን መልመጃ**

1. የማስተባበር ተግባሮችን በአካባቢዎ ውስጥ ካሉ የአገልግሎት አቅራቢዎች እና ተጠቃሚዎች ጋይ ተወያዩ፤
2. በፖሊሲ አውጪዎች እና አገልግሎት አቅራቢዎች በአቅርቦት እና በፍላጎት በኩል ያሉ የሃሳቦች ግልፅነት ይለዩ፤
3. ለዚህ ፕሮጀክት የአስተባባሪ መምረጫ መስፈርት ማጎልበት ይችላሉን?

# 5. የማህበረሰብ የአገልግሎቶች መመዘኛ ካርድ ደረጃዎች፡-

## 5.1. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደት በሚከናወንበት ጊዜ ያሉትን ዋና እና ንዑስ ደረጃዎችን ለተሳታፊዎች ለማስተዋወቅ ነው።
በዚህ መመሪያ ማብቂያ ላይ ተሳታፊዎች፡-

- የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ዋና እና ንዑስ ደረጃ ሂደቶችን ለይቶ ማወቅ፤
- በእያንዳንዱ ደረጃ የሚከናወኑትን ዋና ዋና እንቅስቃሴዎች መለየት፤
- በዚህም መነሻነት የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደትን ማካሄድ ይጠበቅባቸዋል።

## 5.2. ደረጃዎች

የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ /የማ.ተ.ው.መ.ካ/ ሂደት አፈፃፀም የተለያዩ ደረጃዎችን ማለፍ ያለበት ሲሆን እያንዳንዱ ደረጃም የየራሱ ንዑስ ደረጃዎች አሉት። እነዚህም አምስት የካርዱ ሂደት አፈፃፀም ደረጃዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ።

1. ዕቅድ የማዉጣት እና የማዘጋጀት፤
2. የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድን ማጎልበት፤
3. አገልግሎት አቅራቢዎች ራሳቸውን የሚገመግሙበትን መመዘኛ ካርድ ሂደት ማካሄድ፤
4. የጋራ ስብሰባ፤
5. ክትትል እና ተቋማዊነት

### 5.2.1. ዕቅድ ማውጣት እና ማዘጋጀት

በጥሩ ሁኔታ ታቅዶ የተዘጋጀ የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደት ውጤታማ አፈፃፀምን ከሚወስኑት አንዱ ነው። በአብዛኛዎቹ ሁኔታዎች መሠረታዊ የማዘጋጀት ሥራ ማህበረሰቡን ለማሰባሰብ ከሚደረገው እንቅስቃሴ ቀደም ብሎ መጀመር እንዳለበት ይመከራል።

በዚህ ደረጃ እጅግ ወሳኝ የሆኑት ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡-

- መሪ አስተባባሪዎችን መለየት እና ማሰልጠን፤
- ወሰኑን/አድማሱን መለየት፤ ይህ የአገልግሎቱን አድማስ /ለምሳሌ ውሃ፣ ትምህርት፣ ጤና ወዘተ.../ እና የመልክአ ምድራዊ ሽፋኑን /ክልል፣ ወረዳ፣ ቀበሌ/ መለየት፤
- ቁጥጥር የሚደረግበትን የአገልግሎቱን ገፅታ መለየት፤
- ማህበረሰቦቹን በመጀመሪያ በቡድን መመደብ፤
- ከየአካባቢው የሚሳተፉትን ሕዝቦች የናሙና ብዛት መወሰን፤
- የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን እና አቅራቢዎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ከፍተኛ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ሲባል በመስክ ጉብኝቶች፣ ግንዛቤ ለመፍጠር በሚደረጉ ቅስቀሳዎች እና በማግባባት ሥራ ማነቃቃት፤
- የሥራ እቅድ ማጎልበት፤
- አስፈላጊዎቹን ማቴርያሎች እና ሎጂስቲኮች ማዘጋጀት፤
- ግብዓቶችን መለየት፣ ይህ ቁሳዊ ሀብቶችን፣ የአገልግሎት ግብዓቶችን እና የተመረጠው መስክ ማግኘት የሚገባውን ያካትታል። ይህ በአቅራቢያቀው ያለውን መረጃ ለመሰብሰብ እና የአገልግሎቱ ቁልፍ/ወሳኝ ግብዓቶች መገኘታቸውን እና ወይም ጥቅማቸውን በተመለከተ መረጃውን ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።

### 5.2.2. የማህበረሰብ የአገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደትን ማጎልበት፡-

በዚህ የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ውስጥ እጅግ በጣም ወሳኙ ደረጃ ነው። ይህም የተለያዩ ግንዛቤዎችና አመለካከቶች ያላቸው ማህበረሰባዊ ቡድኖችን ፍላጎትና መብቶችን ስለሚያካትት ቁጥጥር እና ክትትል ስለሚያደርግበት አገልግሎት እና አካባቢ የተከማቸ መረጃን በጥንቃቄ እና በትጋት መያዝን ይጠይቃል። በዚህ ደረጃ ሥር ከዚህ በታች ያሉትን የተለያዩ ንዑስ ደረጃዎች በጥብቅ መከተል ይመከራል።

1. ማህበረሰብን ለማሰባሰብ የሚረዱ ንዑስ ደረጃዎች፡-

- ለማህበረሰቡ ስለ አላማው እና ዘዴው አጭር መግለጫ መስጠት፤
- ተሳታፊዎችን ለውይይት በሚያመች ሁኔታ በቡድን /ለምሳሌ በሥርዓተ ፆታ፣ በእድሜ፣ በማህበራዊ አደረጃጀት፣ በገቢ ወዘተ.../ መከፋፈል፤
- በእያንዳንዱ ቡድን ስብሰባውን የሚመራ እና ሪፖርት የሚመዘግብ መመደብ፤/በአንድ ቡድን ሁለት ሰዎች ማለትም መሪ እና ማስታወሻ የሚይዝ/

## 2. ግብዓት የማስገባት መለኪያን የማጎልበት ንዑስ ደረጃዎች

- ለቡድኑ ግብዓትን ወደ አገልግሎቱ ማስገቢያ ዓላማን ማብራራት፤
- የግብዓት መረጃ /ግብዓት ማግኘት ላይ መረጃ 1 አግኝቶ ወደዚህ ለማስገባት ከአገልግሎት አቅራቢዎች ጋር ቃለመጠይቆችን ማካሄድ /ማሰባሰብ፤
- ለግብዓት አመልካቾች ውይይት ከመካሄዱ እና ስምምነቶች ላይ ከመድረሱ በፊት በግብዓት ማግኘት መብት ወይም በአንድ የተለየ አገልግሎት ላይ መረጃ ማቅረብ።

| ግብዓት | መረጃ የማግኘት መብት /በአገልግሎት ኋላፊነት እና ተግባር፣ ብሔራዊ መስፈርት ወዘተ… ላይ በዝርዝር እንደተመለከተው/ | ተጨባጭ /የማህበረሰቡ ግንዛቤ፣ በእውን ምንድነው/ | መግለጫ/ማስረጃ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |

### የግብዓት ማስገቢያ ማስታወሻ፦

በውሃ አቅርቦት እና በመስኖ ኤክስቴንሽን ዘርፎች ብቃት ያለው አገልግሎት መቅረቡን ለማረጋገጥ ግብዓቶች በአንድ አገልግሎት ማቅረቢያ ቦታ የሚመደቡ ሀብቶች ናቸው። እነዚህም፦

- ቁሳዊ ሀብቶች እና የአገልግሎት ግብዓቶች ከፌደራል፣ ክልል፣ ወረዳና አካባቢዎች የሚደረገውን ፍሰት መቆጣጠርን ይመለከታል፣
- በዋናነት የማግኘት መብቶች ከብሄራዊ በጀቶች፣ የፕሮጀክቶች ሰነድ፣ ብሔራዊ ፖሊሲዎች እና ደረጃቸውን የጠበቁ ደንቦች ላይ የሚሰጡ አስተያየቶችን ይመለከታል።
- ቁሳዊ ሀብቶች፣ እንደ የውሃ ፓንፖች፣ የመስኖ መሳቢያዎች ወዘተ… ናቸው።
- የአገልግሎት ግብዓት፣ እንደ ሠራተኞች፣ የውሃ ኮሚቴ፣ የኤክስቴንሽን ሠራተኞች ወዘተ፤
- የማህበረሰብ ግንዛቤ በግብዓቶቹ እና እንደመብት በሚያገኙዋቸው ላይ የማህበረሰቦቹ እውነታዎችን ይመለከታል።

**የቡድን መልመጃ**
ተሳታፊዎች ከተወከሉበት ወረዳ መነሻ አድርጎ በመክፈል በትምህርት እና በጤና ላይ የግብዓት ቁጥጥር ማጎልበት።
መልመጃው ተሳታፊዎች ስለ ወረዳዎቻቸው እውቀት እንዲኖራአው ይጠይቃል።

ለምሳሌ እያንዳንዱ ግብዓትን የማስገባት እና የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደት ለ800 ሰዎች በቀን 100 ሰዎች እና በአንድ ስብሰባ 25 ሰዎች ሰባት ስምንት ቀን ይወስዳል። /ሁለት ስብሰባዎች ጠዋት፣ ሁለት ስብሰባዎች ከሰዓት በኋላ/

3. የማህበረሰብ አገልግሎት መመዘኛ ካርድ ሂደትን ማጎልበት

❖ ጉዳዮችን ማመንጨት፤ /ጭብጦች ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሊመነጩ ይችላሉ/፦
  - ነገሮች በአገልግሎት ወይም መርሐ ግብሩ እንዴት እየሄደ ነው?
  - በጥሩ ሁኔታ እየተካሄዱ ያሉት መርሀ ግብሮች ወይም አገልግሎቶች የትኞቹ ናቸው? በደንብ የማይሰሩትስ?

❖ ለችግሮች ቅድሚያ ማውጣት፣ /በቅደም ተከተል መታየት የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ መስማማት።/

ምሳሌ

| ችግሮች | ቅደም ተከተል | ምክንያት |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

❖ የመጀመሪያ ስብሰባ ማብቂያ፤

ችግሮች ከመነጩ እና ቅድሚያ ያላቸውን የመለየቱ ሥራ ከተሰራ በኋላ የመጀመሪያው ቀን ስብሰባ ማብቂያ ይሆናል። የቀኑን ተጨባጭ ሥራ ከማብቃቱ በፊት የሚከተሉት መከናወን አለባቸው።

- አጠቃላይ ስብሰባ /ሁሉንም ቡድኖች በአንድነት/እንደገና መጥራት፣
- ቅድሚያ የተሰጣቸውን ጉዳዮች አመላካቾችን ለማጎልበት መረጃውን ወደ ጽ/ቤት መልሰው እንደሚወስዱ ያብራሩ፣
- በሚቀጥለው ስብሰባ ጉዳዮቹ /በአመላካችነት የሚቀርቡት/የሚመዘገቡ መሆናቸውን መስማማት፣
- ተመሳሳይ /አንድ ዓይነት/ ቡድኖች ከተመሰሳይ ሰዎች ጋር ለምዝገባው ልምምድ መገኘት እንዳለባቸው ግልፅ ማድረግ።

❖ አመላካቾችን ማጎልበት፦

- ወደ ጽ/ቤቱ መመለስ፣
- ሁሉም ቡድኖች በተገኙበት ባመነጩት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ መለዋወጥ፣

- ከተለያዩ ቡድኖች የመጡትን ጉዳዮች በአንድነት ካሰባሰቡ በኋላ ቁጥጥር የሚደረግባቸውንና አገልግሎቱን የሚወክሉ የጋራ ጉዳዮችን ማውጣት፣
- ዋና ዋና ጉዳዮችን መለየት እና ከነዚህም አመለካቾችን ማጎልበት ከእያንዳንዱ አመላካች ጋር የሚያያዙ ጉዳዮችን መዘርዘር፣
- አመላካቾችን ቁጥጥር በሚደረግባቸው /ጥራት፣ መገኘት፣ በቂነት እና ብቃት/ አድማስ መመደብ።

## ❖ የለውጥ /የእድገት/ መገምገሚያ ነጥቦች ማዘጋጀት

በዚህ ደረጃ ሥር እጅግ አስፈላጊው ተግባር ለመገምገሚያ እንዲውሉ ተለይተው ከታወቁ የማሳያ ነጥቦች /indicators/ ላይ የለውጥ ወይም የእድገት መለኪያ ማዘጋጀት ነው።

የለውጥ /የእድገት መገምገሚያ ምሳሌ፡-

<table>
<tr><td colspan="3">የቡድን ሥም--------------- ቀን--------------- ክትትል የተደረገበት------------- ወረዳ-------------- ቀበሌ--------------- አገልግሎት</td></tr>
<tr><td>አመልካች ነጥቦች</td><td>ነጥብ</td><td>ምክንያት /አስተያየት/</td></tr>
<tr><td>የትምህርት ጥራት</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>የክፍሉ ሠራተኞች ጤናማ ጥረት</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td>የሴቶች ተሳትፎ</td><td></td><td></td></tr>
</table>

ማሳያ ነጥቦች እና መለኪያቸውን አዘጋጅተን ካጠናቀቅን በኋላ በቀጥታ የምንመለሰው ወደ ማህበረሰቡ ነው።

## ❖ ከማህበረሰቡ ጋር ግምገማ ማካሄድ፡-

የሚከተሉት ተግባራት በዚህ ሥር ይከናወናሉ።

- ተሳታፊዎችን በተለያዩ የትኩረት ቡድኖች መከፋፈል፣ /በመጀመሪያው የስበሰባ ቀን አንድ ዓይነት ሀሳብ ያቀረቡትን ሰዎች በአንድ ዓይነት ቡድን ውስጥ መመደብ/
- ለእያንዳንዱ ቡድን የተዘጋጁ ማሳያ ነጥቦችን መስጠት፣

**አፈፃፀምን መገምገም፡-** ግምገማ በዓይነት ማለትም በጣም ዝቅተኛ፣ ዝቅተኛ፣ ምንም የማይል፣ ጥሩ፣ በጣም ጥሩ ተብሎ የሚገለጽ መሆን አለበት። አፈፃፀምን ለመገምገም አሀዛዊ ደረጃዎችን መጠቀም ነው። ይህም ከ1-5 ወይም ከ0-100% ሊሆን ይችላል። የቡድኑ አባላት በነጥቦች ላይ በድምፅ ወይም ተመራጭ በሚሆነው ሊስማሙ ይችላሉ።

- ለሚሰጠው ለእየንዳንዱ ነጥብ ማብራሪያና ለሚደረጉ ማሻሻያዎችም አስተያየቶች ያስፈልጋሉ፣

**ማስገንዘቢያ፡-** ለመለኪያዎች ነጥብ ሰጥቶ ማጠናቀቅ የዕለቱ የመጨረሻ ተግባር ነው። ይሁን እንጂ ቡድኖቹ ከመበተናቸው በፊት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውኑ፣

- ሁሉንም ቡድኖች በአንድ ላይ መሰብሰብ፣
- የቡድናቸውን አመለካከት የተመረጡባቸው ቀናት በማንፀባረቅ የተጠናቀረ ውጤት የሚያስገኙ ከእያንዳንዱ ቡድን 2 ወይም3 ተወካዮችን መምረጥ፣
- ማህበረሰቡን ስለ ጋራ ስብሰባ እና ስለሚካሄድበት ቀን ማሳወቅ፣
- ወደ ቢሮ በመመለስ የእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን ነጥቦችን መመዝገቢያ በማዘጋጀት ዉጤቱን ማጠናቀር /ከእያንዳንዱ ማሳያ ነጥብ አንፃር የተሰጠ ነጥብ/
- በተቀጠረው ዕለት አስተባባሪዎች የተወካዮችን ቅፅ ከእያንዳንዱ የትኩረት ቡድን ማግኘት አለባቸው፣
- ተሳታፊዎች ከእያንዳንዱ የቡድናቸው አባላት ጋር ነጥብ እንዲጋሩ እና ነጥቦቹ መለኪያ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ፣
- አስተባባሪዎቹ በውይይት የተነሱትን ጥያቄዎች ማለትም የተለያዩ ነጥቦችን በመመልከት
    - ትክክለኛው ምስል ምንድነው?
    - የትኞቹ ነጥቦች ሁሉንም ነጥቦች እና እውነተኛውን ሁኔታ ይወክላሉ?

ይህም ሁሉንም የሚወክሉ ነጥቦችን አማካዩን በመውሰድ ወይም ተመራጭ በሆነው በመስማማት ለማግኘት ነው።

ለምሳሌ የተጠናቀሩ ነጥቦች መለኪያ፤

| ማሳያዎች | የቡድን ተኮር ዉጤቶች | | | የተጠናቀረ ነጥብ |
|---|---|---|---|---|
| | የቡድን “ሀ” ነጥብ | የቡድን “ለ” ነጥብ | የቡድን “ሐ” ነጥብ | |
| ማሳያ 1 | X | Y | Z | S |
| ማሳያ 2 | a | a | c | a |

**<u>የቡድን ሥራ</u>**

ሁለት ቡድኖች መመስረት ማለትም፣ የትምህርትና የጤና በሚል ሕብረተሰቡን ለመገምገሚያ ማዘጋጀት። ቡድኑ ከላይ የተጠቀሱትን እያንዳንዱን ደረጃና ቅደም ተከተል አጥብቆ እንዲከተል መምከርና ሰንጠረዥ ማዘጋጀት ይገባል።

### 5.2.3. አገልግሎት ሰጪዎች ራሳቸውን የሚገመገሙበት መገምገሚያ ካርድ፡-

ይህ ደረጃ አገልግሎት ሰጪዎች አገልግሎታቸውን እንዲገመግሙ ያደርጋቸዋል። አሰራሩ ከማህበረሰብ መገምገሚያ ነጥብ ጋር ይነስም ይብዛ አንድ ዓይነት ነው። ይሁን እንጂ መገምገሚያው ሙሉ በሙሉ አንድ ዓይነት አይደለም።

በዚህ አሰራር የአባላት ብዛት /መጠን/ ትንሽ በመሆኑ እና ከአንድ አይነት ተቋም ስለሚመጡ ቡድን መፍጠሩ አያስፈልግም። ነገር ግን ተሳታፊዎች ብዙ ከሆኑ ቡድን መፍጠር እና የቡድን ነጥቦችንም ማጠናከር ያስፈልጋል።

አሰራሩ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች መገምገሚያ ከተዘጋጀዉ ጋር በአብዛኛው ተመሳሳይ ነው። ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ አንድ አይነት አለመሆኑን ማስታወስ ያሻል። የአሰራር ደረጃዎች አጭር ናቸው። ምክንያቱም አገልግሎት ሰጪዎች በአንድ ቡድን ከተዋቀሩ ቡድን መመስረት እና ነጥብ ማጠናቀር ባለማስፈለጉ አስተባባሪው ማሳያዎችን ለማዘጋጀት እና ለማሳያዎችም ውጤት ለመስጠት በመጀመሪያው ቀን ይከናወናል ብሎ እስካሰበ ድረስ ነው። በመሆኑም የአሰራር ደረጃዎችን ካለው ሁኔታ አኳያ መመልከት ያስፈልጋል። የአገልግሎት ሰጪዎችን መገምገሚያ ለማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች የተጠቀምነውን አሰራር መከተል ከዚያም በላይ አጭር ማድረግ /ማሳጠር/ ይቻላል።

ይሁን እንጂ አሰራሩ ግልጽ እንዲሆን ሁሉንም የአሰራር ደረጃዎች የተጠቃሚዎችን መገምገሚያ መግለጽ ጠቃሚ ነው። በዚህ ስር የሚከተሉትን የአሰራር ደረጃዎች መከተል ይገባል።

## 1. አገልግሎት ሰጪዎችን ማደራጀት

- የግምገማ መልመጃን የሚመራ አወያይ መምረጥ /በቡድን አባላት የሚከበርና የሚታመን መሪና ማስታወሻ ያዥ/
- ለቡድኑ የመልመጃውን ጥቅምና አገልግሎት መግለፅ የቡድኑ አባላቱ ግለሰቦችን እና ሰዎችን መከተል እንደሌለባቸው ግን ስልቶችን፣ መዋቅሮችን፣ ፖሊሲዎችን እና አሰራሮችን በሚገባ እንዲያጤኑ መምከር
- አስተባባሪው ስለማህበረሰብ ግምገማ እንዲያብራራ ማድረግ፣

## 2. የአገልግሎት ሰጪዎችን መገምገሚያ ማዘጋጀት

- ቀዳሚ ትኩረት፡- በአገልግሎት ሰጭዎች የቀረቡ ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥቶ ቅደም ተከተል ማስያዝ፣
- ከማህበረሰብ ጋር ተመሳሳይ አመልካች ነጥቦችን መጠቀም፡- የተለየ የነጥብ አሰጣጥ መንገድ መጠቀም፣
- የመለኪያ ነጥብ ሰንጠረዥ ማዘጋጀት፡- የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን መለኪያ አዘገጃጀት ተመልከት፣
- የአገልግሎት ሰጪዎች እራሳቸውን የሚገመግሙበት የመገምገሚያ ነጥብ ማዘጋጀት፡- የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ለመገምገም የተጠቀሙበትን አሰራሮች ተጠቀም፣

በዚህ ስር የሚከተሉትን ማከናወን ይገባል፡-

- በነጥብ አሰጣጥ ላይ መስማማት /ለማህበረሰብ መገምገሚያ የተጠቀመውን የነጥብ አሰጣጥ ስልት አልፎ አልፎ እንደሚጠቀም ማስታወስ/
- ለእያንዳንዱ ማሳያ ነጥብ አገልግሎት ሰጪዎች በተወሰነው የነጥብ አሰጣጥ ስልት ነጥብ እንደሚሰጡ በመጠየቅ መጀመር፣ /ቡድኑ በሰንጠረዥ ላይ ከመፃፉ በፊት በነጥቡ ላይ ሊስማማ ይገባል/

## የመለኪያ ሰንጠረዥ

| ማሳያዎች | ነጥብ | ምክንያት /አስተያየት/ |
|---|---|---|
| አመልካች 1 | | |
| አመልካች 2 | | |
| አመልካች 3 | | |

❖ የአገልግሎት ሰጪዎች ግምገማ ማጠናቀር፡-

ከአንድ በላይ ቡድኖች ካሉ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን የግምገማ ነጥብ ለማጠናቀር የተጠቀምንበትን አሰራር እንከተላለን።

**የቡድን መልመጃ**

- ተሳታፊዎችን በትኩረት ቡድን መከፈል፣ /ትምህርት እና ጤና/
- የአገልግሎት ሰጪዎችን መገምገሚያ ነጥብ ማዘጋጀት፣
- እያንዳንዱ ቡድን ዝግጅቱን እንዲያቀርብ ማድረግ፣

5.2.4. የጋራ ስብሰባ፡-

ይህ መድረክ የአገልግሎት ሰጪዎች እና የአገልግሎት ተጠቃሚዎች በአንድ በተወሰነ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ገንቢ ውይይት የሚያደርጉበት የጋራ ስብሰባ ነው። በስብሰባው ላይ የእያንዳንዱን ወገን የግምገማ ውጤት ማሳየት ያስፈልጋል። ስብሰባው ተጨባጭ ማሻሻያ፣ የተግባር እቅዶች የሚቀየሱበት እና ስምምነት ለተደረገባቸው እቅዶች ስኬት ክትትል እና ጥረት የሚደረግበት ሊሆን ይገባል። በዚህ አሰራር መሰረት ተፈላጊ ሰዎች ማለትም ውሳኔ ሰጪዎች፣ የህዝብ እና የሲጋሽ ተወካዮች ወዘተ… በስብሰባው ላይ እንዲገኙ አስፈላጊው ጥረት ሁሉ መደረግ አለበት።

1. የጋራ የግንኙነት ስብሰባ ማካሄድ፦

- የጋራ ስበሰባው ጥሩ ችሎታ እና ልምድ ባለው አስተባባሪ እንደሚካሄድ ማረጋገጥ፣
- ዓላማውን መግለጽ፣
- የስብሰባውን የአካሄድ ስልት መግለጽ፣ (በአገልግሎት ሰጪዎችና ተጠቃሚዎች መካከል አሳታፊ ውይይት)
- የማህበረሰብ ተወካዮች የተጠናቀሩ የግምገማ ነጥቦችን ማቅረብ፤ (በዝቅተኛ ውጤቶች እንዴት ማሻሻል እንደሚገባ እና ከፍተኛ ውጤቶችን እንዴት መጠበቅ የሚቻልበትን አስተያየት)
- የአገልግሎት ሰጪዎች ተወካዮች የቡድኑን ነጥብ ማቅረብ /ከአገልግሎት ተጠቃሚዎች ተወካዮች የቀረቡ አስተያየቶችን እና የራሳቸውን አስተያየቶች ጨምረው/፣
- አሳታፊ ውይይት /ንግግር እና ጥያቄዎችን መክፈት፣
- ከውይይቱም አሳሳቢ እና አደገኛ ጉዳዮችን መለየት፣
- ለአንገብጋቢ ጉዳዮች ትኩረት መስጠት፣

2. የጋራ ተግባር እቅድ ማዘጋጀት፦

- ለጋራ ጉዳዮች የቅድሚያ ትኩረት መስጠት፣
- ቅድሚያ ትኩረት የተሰጣቸውን ጉዳዮች በቅደም ተከተል ተሳታፊዎች ለማሻሻያ ከሰጡት አስተያየቶች ጋር በቻርት ውስጥ ማስፈር፣
- ለማሻሻያ የተሰጡ አስተያየቶች ተጨባጭ እና ሊለኩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣
- ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠባቸው ነጥቦችን አንድ ላይ መመደብ እና በሁሉም ላይ መስማማት (ስም/ርዕስ)
- በእያንዳንዱ ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶ በቀረበው መልእክት ላይ መወያየት እና በለውጥ መለኪያ ሰንጠረዥ ውስጥ ማስቀመጥ፣

የለውጥ መለኪያ ሰንጠረዥ ማዘጋጀት (ሁሉም እንዲያየው በቻርት ላይ ማስፈር)

| ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው መልእክት | ተግባር (ጉዳዩን ለማከናወን የሚያስፈልግ) | ማነው ተግባሩን የሚመራው? | ከማን ጋር? /ስምና ተቋም/ | መቼ? /ተጨባጭ ጊዜ/ | ማስታወሻ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |
| | | | | | |

### 5.2.5. ክትትል እና ተቋማዊነት

የዚህ ዋናው አላማ የመጀመሪያዉ ዙር ግምገማ ከተደረገ እና የጋራ የተግባር እቅድ ከተዘጋጀ በኋላ መቆም የሌለበት መሆኑን ማሳየት ነው። ተደጋጋሚ ዙር ግምገማ በማድረግ ተግባሩን ተቋማዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በግምገማ የሚሰጠው መረጃም ዘላቂነት ባለው መልኩ አገልግሎት ላይ ሊውል ይገባል።

ይህ በዋናነት መረጃን ማሰራጨት፣ የጋራ የተግባር እቅድ መተግበር እና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻልን በተደጋጋሚ ዙር ግምገማ መፈተሽን ይመለከታል። በዚህ ስር መረጃን በተገኘው ዘዴ ማሰራጨት፣ መደበኛ የክትትል ዘዴዎች ለማስተዋወቅ፣ የአፈጻጸም ደረጃ ለማውጣትና ለማዘጋጀት ወ.ዘ.ተ አስፈላጊ ነው።

**የማስመሰል ጨዋታ**

- የትምህርት ወይም የጤና አገልግሎት ዘርፍን መምረጥ፣
- ተሳታፊዎችን ለሁለት መክፈል /አገልግሎት ሰጪ (አቅራቢ) እና አገልግሎት ተጠቃሚ/
- የግንኙነት ስብሰባን መለማመድ፣

# ማጣቀሻ ጽሑፎች/ዋቢ መጽሀፍት


1. Water aid Ghana Briefing Paper (2004) No.4"Tin Community Score Card Approach.
2. የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር "Ethiopia Build and Progress. A Plan for Accelerated Sustained Development to End Poverty (PASDEP), 2005/06-2009/10, September, 2006."
3. የጆርጅ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ (2000) HerbertV Moris in the Globalization and Human Right Law, The role of International Finance Institution in Promoting Human Right, Vol33No.1.
4. Overseas Development Institute: Right Based Approach to Development (http://www.odi.org.uk).
5. UNDP, Poverty Eradication and Human Right 2003, www.undp.org
6. ዜማ ሴቶች ለፍትሕ ማህበር A Practical Guide to Implementing the Community Score Card in Ethiopia,"2008
7. የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የ1987 ህገ-መንግስት
8. Community Score Card Process, http://info.worldbank.org/etools/docs/94570/Tanz_1103/Ta_1103/the Community Scorecard, Nov.03PDF
9. Participatory Approaches: http://www.sanico.net/thles/toicintro.php3
10. Japan Distance Corporation Agency (JICA) "Participatory Development and Good Governance" http://www.gdrc.org/u-9000/doc-jicd_99,html.